# መዝቀጥ እንደ አብይ አህመድ – እውነቱ ቢሆን

April 5, 2023



*<..እኛ አገር ማፍረስ ከፈለግን ማን ነው የሚያስቆመን? የሚያቆመን አለን?..> ከህግ በላይ የሆነው አብይ ባለፈው ሳምንት ለሙቱ ፓርላማ ከተናገረው የተወሰደ*

(እውነቱ ቢሆን)

በአለም ላይ መቋጫ በሌለው ውሸት ተጀቡኖ እልቂትን እየደገሰና ለራሱ ህዝብ ሞት ደስታን እየፈጠረ ስለ ራሱ ታላቅነት ብቻ ቅዠት እየቃዠ የሚኖር በቁሙ የዘቀጠ እንደ አብይ አህመድ ያለ ሰው ተፈልጎ አይገኝም፡፡

የወያኔ 27 አመታት አገዛዝ በህዝቡ ትግል ተሽቅንጥሮ ወያኔ ከመሀል አገር ተባርሮ ወደ መቀሌ ሲሄድ አጬናባሪው አብይ አህመድ ደመቀ መኮነንንም ፣ ገዱ አንዳርጋቸውንና ለማ መገርሳንም “ቁጬ” ሰርቷቸው አብይ በመሪነት ቦታ ላይ ተቀመጠ፡፡ ድራማው ታሪካዊ ነበር፡፡ የአማራ ክልል ህዝብ ያኔም በወያኔ ተንገሽግሾ ስለነበረ ሲሆን ብዙ በደሎችና ግፎች ደርሰውበታል፡፡ ወያኔ በህዝብ ትግል ተሽቀንጥሮ ከማእከል ሲባረር

የአማራ ክልል ህዝብ ግልብጥ ብሎ ወጥቶ ለአብይ አህመድ ከማንም ቀድሞ ደስታውን በይፋ ገለጸለት፡፤ በውጭ አገራትም በተለይ በአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ ዲያስፖራው ንቅንቅ ብሎ ወጥቶ አብይን ደግፎ ደስታውን ገለጸ፡፡ ያ ሁሉ የአብይን ማንነት ካለማወቅና የወያኔን ድርጊት ከመጥላት የመነጨ ነበር፡፡ አይፈረድበትም፡፡ እዚህ ላይ “” አረሱት”” በሚል መጠሪያ ዘፈኑ የሚታወቀውን አርቲስት ፋሲል ደመወዜ ለአብይ አህመድ ያኔ የገጠመውን ግጥም እንመልከት፡፡

<< አሼሼ አሼሼ ……አብይ መጣልን ከመሼ>>

ታዋቂው አርቲስት ፋሲል ደመወዜ ይህንን ግጥም የያዘ ዜማ ለአብይ አህመድ ያኔ ከመዝፈኑ ከአመታት በፊት ወያኔ ከአማራው በጉልበት ወልቃይትንና ራያን ወስዶ ወደ ትግራይ ክልሎት ስለነበረ የያኔውን የአማራን ህዝብ ሲሰቃይ የነበረበትን ሁኔታ ለመግለጽ የገጠመውን የሽለላ ግጥም አሁንም ላንሳ፡፡ ግጥሙ ይህ ነበር፡፡

<< አረሱት ያውም የእኛን መሬት ያውም የእኛን እጣ ……..        እነርሱ ምን ያርጉ ከእኛ ሰው ሲታጣ>>>

ጥላሁን ገሰሰ በዜማው እንዳለው አንዳንድ ነገሮች ይገርማሉ፡፡አሁንም ይሄዉና ራያና ወልቃይት ዳግም በተረኛው ኦሮሙማም ጊዜ የእልቂት መንስኤ ሊሆኑ ጫፍ ደርሰዋ፤ል፡፡ አንድ ነገር ግን በእርግጠንነት መናገር ይቻላል;፡፡ ነብይነት አይደለም፡፡ ወልቃይትና ራያ ቢፈልግ በካሽሚርነት ይመሰል፡፡ ቢፈልግም በጋዛ ሰርጥነት ይመሰል፡፡ አንድ ነገር ግን እርግጥ ነው፡፡ አማራው ምንጊዜም እነዚህን እጅግ ለም የሆኑ ታሪካዊ ርስቶቹን ለወያኔ አሳልፎ አይሰጥም፡፡ በፈለገው ስርአት ትግሉና ዉጊያው የፈለገውን ጊዜ ይውሰድ እንጅ መሬቶቹ የአማራ ርስቶች ሆነው ይቀራሉ፡፡

አብይ አህመድን ህዝቡ እንዴት ያየዋል የሚለውን እንፈትሽ፡፡ እንዳው በሞቴ አብይን ምን ትሉታላችሁ?? አታላይ፣ አጭበርባሪ፣ ውሸታም፣ ቁጭ በሉ፣ ምስኪን፣ ጥሩ ልብ ያለው ግን አቅመ ቢስ፣ ተስፈኛ፣ ፈላጭ ቆራጭ ድክታተር፣ ግጭት ጠማቂ፣ ሰው ጠል፣ እውር ድንበሩ የጠፋበት ግራ የገባው ባተሌ፣ ሰይጣን፣ ጋኔን፣ ደም የጠማው አውሬ፣ ራሱን ጠልፎ የጣለ መካሪ የለሽ መሪ፣ ጥጋብ የነፋው ዱርዬ፣ እናቶች የሚጸልዩለት ጥሩ ሰው፣ ሀይማኖተኛ፣ ምሁር፣ ሩህሩህ፣ ጨካኝና አረመኔ ሰው…… ወዘተ??? የፈለጋችሁትን ደርድሩ፡፡

በአገሪቱ ውስጥ መሬት ላይ ካለው ተጨባጭ፣ የሚታይና የሚዳሰስ እውነታ አንጻርና ከ120 ሚሊዮኑ ኢትዮጵያዊያን ከሚገፉት የመከራ ኑሮና የመከራ ህይወት አንጻር ህዝቡ ስለ”መሪ” ተብየው ስለአብይ አህመድ ስብእና ምን ይል ይሆን?? ከአገሪት ውድቀትናተስፋዋ የቸለመባት አገር ከመሆን አኳያ ብዙሀኑ

ኢትዮጵያዊ ህዝቡንም አገሪቱንም ለዚህ ያበቃትን አብይ አህመድን ምን ይለው ይሆን??

ህዝቡ የውሸት ቋት በሆነው በስም የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በሚባለው በተግባር ግን የኦሮሙማው ብልጽግና ቴሌቪዥን ፕሮፓጋንዳ ማሽን በሆነው <<የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን>>በየቀኑ አብይ የሚለውን ስም ሲሰማና ምስሉን በየቀኑ እንዲያይ ስደረግ ህዝቡ ምን ይል ይሆን??

ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጧል ቢሆንበትም ህዝቡ የትናንቱን የወያኔ የስቃይ ጊዜ ከአሁኑ የኦሮሙማ የእልቂትና የገሀነም ወቅት ጋር ሲያያወዳደረው አሁን በመኖርና ባለመኖር መካከል ሆኖ የሚያቃትተው ህዝብ ስለ ኦሮሙማ፣ ስለኬኛ ፖለቲካና የስቃዩ ሁሉ ምንጭ ስለሆነው ግለሰብ ስለ አብይ አህመድ ምን ይሰማው ይሆን?

የህዝቡ ቁጥር በመቶኛ ቢሰላና አብዛኛው ህዝብ ምናልባትም 90% እና ከዚያም በላይ ያለው ህዝብ አብይን የት ይመድበዋል ብላችሁ ትገምታላችሁ?? ታሪክስ??

አለም ብዙ ድክታተሮችን አይታለች፡፡ ታሪክም ይህንኑ መዝግባ ይዛለች፡፡ ለዚሁም የጀርመኑ ሂትለርና የጣሊያኑ ሙሶሎኒ ዋና ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ሌሎችም ነበሩ፡፤ አሁንም አሉ፡፡ በመሰረቱ ድክታተር የሆነ ሰው ከስሩ ያሉት ሰወች የሚሰግዱለት እንጅ ሀሳብ አቅርበው የሚያማክሩት፣ እንዲያ ሲልም አይበጅም፣ ይቅርብህ፣ አይሁን የሚሉት ፣ግፋ ሲልም በሀሳብ የሚሞግቱት አይደሉም፡፤ በጭራሽ!!

አብይ አህመድ ስብእናው የዘቀጠ ብቻ ሳይሆን ሰው የሆነ ፍጡር ይፈጽማቸዋል ተብለው በማይገመቱ አሰቃቂና ሰቅጣጭ የወንጀል ስራወቹ ተጨመላልቆና ገምቶ የከረፋ ሰው ነው፡፡ ግድያንን በሚለከት ካስገደላቸውታዋቂ ሰውች ውስጥ ብቻ ጥቂቶቹን እንጥቀስ፡- ኢንጅነር ስመኘው በቀለ፣ ጀኔራል አሳምነው ጽጌ፣ ዶ/ር አምባቸው መኮንን፣ አቶ ምግባሩ ከበደ፣ ጀኔራል ጳአረ መኮንን፣ አቶ አዳሙ ረታ ወዘተ (አብዛኛው አማራወች) ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ሰወች ለስልጣኔ ያሰጉኛል ብሎ ራሱ በቀጥታ ያስገደላቸው እንቁ የኢትዮጵያ ልጆች ናቸው፡፡ ስለነዚህ ታዋቂ ሰወች አሟሟት እስካሁን ምን ተደረገ??ምን ማታራት ተካሄደ?? ምንስ እርምጃ ተወሰደ??? ውሻን ያነሳ ዉሾ ሆኖ ቀረ፡፡ እርሱ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆኖ የተካሄዱት በአገርና በህዝብ ላይ የተካሄዱት ዘግናኝ ድርጊቶች ብዙ ናቸው፡፡ ምሳሌ አፈናን በሚመለከት አንድ ምሳሌን ብቻ እንጥቀስ፡- ምስኪን የሆኑ ከ19 በላይ የአማራ ሴት ዩኒቨርሲቲ ተማሪወች በአማራነታቸው ታፍነው እርሱ በሚመራው የአክራሪ ኦሮሙማወች አንዱ ከንፍ እንዲወሰዱ አስደርጎ እስከዛሬ ድረስ እነዚያ ሴት ተማሪወች ወሬያቸው ተዳፍኖ እንዲቀር አድርጓል፡፤

በሚስቱም በኩል ሆነ በራሱ በኩል ከውስጥም ይሁን ከውጭ ምንጩ እንደኤትና ከየት እንደእሆነ ያልተገለጸ አጠቀቀሙም ብሄራዊ ባንኩም ሆነ የአገሪቱ ገንዘብ ሚኒስቴር ያልመዘገበው የማያውቀውና የማይቆጣጠረው ከፍተኛ ገንዘብ ይግበሰበሳል፡፡ ዘራፊነቱንና፣ በተለያዩ የኬኛወቹ ክንፎች በመንጋወች አዘራፊነቱን፣ ጨፍጫፊ አስጨፍጫፊነቱን በሚመለከት ብዙ መረጃወችና ማስረጃወች ተሰደረው የፍርድ ቀንን እየተጠባበቁ ነው፡፡ እርሱ ግን በወንጀል ስለመጨመላለቁ አሁን ላይ ዘግይቶ የባነነ ቢመስልም አሜሪካ “”ጥላ ጠለላ”” ሆና ታድነኛለች በሚል ተስፋቢስነት ሙልጭ ብሎና ጠቅልሎ ወደለየለት አገር ሽያጭ ገብቷል፡፡

አገሪቱ ከድንበር 50 ኪሎ ሜትር ወደ ውስጥ ዘልቆ በሱዳን ተወርራ፣ የእርስ በእርስ እልቂቱ በየቀኑ ሙቶወችንና ሽህወችን እየበላ፣አሁንም ዜጎች በማንነታቸው እየተለዩ እየተገደሉ እየተፈናቀሉ ቤቶቻቸው ባላያቸው ላይ በሽመልስ አብዲሳ አፍራሽ ቡድን ቤቶቻቸው እንዲፈርስባቸው እየተደረገ አብይ አህመድ ግን አሁንም አይኑን በጨው ታጥቦ ወጥቶ ኢትዮጵያ አትፈርስም ይለናል፡፡ አብይ አህመድ ግን ኢትዮጵያ አድጋለች ፣ ተመንድጋለች በልጽጋለች፣ዲሞክራሲን አስፍናለች ለሁሉም እኩል ሆና በእኔ አገዛዝ ምቹ አገር ሆናልናለች ይለናል፡፡ ይህ ሁሉ ሀሰት ነው፡፡ ፍብረካ ነው፡፡ ውሸት ነው፡፡ ማታለል ነው፡፡ ሰውየው ግን ትናንትም ዛሬም በሀሰት ይቀደዳል ፣ እንደገናም አንድ ቦታ ላይ ድንገት ይከሰትና እንደ አቡጀዲ ጣቃ በውሸት “ይተረተራል”፡፡

ስለመተርተሩ አንዲት የቅርብ ቀናት ገጠመኝን ላንሳላችሁ፡፡ ባለፈው ሳምንት በአማራውላይ የሚሰራው ግፍ ሞልቶ የፈሰሰ መሆኑን ህዝቡ በቁጣ ለመግለጽ የህዝብ የተቃውሞ ሰልፍ በተጠራበት እለት በጎንደር ከተማ ፋሲሊደስ ቤተመንግስትን በአስወጊው ግለሰብ በዲያቆን ዳናኤል ክብረት አስጎብንነት ጉብኝት ሲያደርግ የተናገረው ትንሽ ፈገግ ያስኘ ነበር፡፡አብይ በቦታው ላይ እንዲዚህ አለ፡፡ “....’አባቶቻችን የሰሯቸውን የታሪክና የስልጣኔ አሻራወችእያለ ሲዘረዝር የአክሱም፣ የዛጉየና የፋሲለደስ ብሎ ሶስቱን ከጠቀሰ በኋላ የፋስሊደስ ቤተመንግስት ሲሰራ እነ እንትና ከዚህ እነ እንትና ከዚያ መጥተው ተሳትፈዋል ብሎ ገለጸ፡፡ ኦሮሞም በወታደርነት በጥበቃ ተሰማርቶ አስተዋጾ አድርጓል >> ብሎት አረፈው፡፡ ከዚያስ ለምን “”አባቶቻችን”’ ብሎ ጅምሮ በኦሮሚያ ላሰሩት የስልጣኔና የታሪክ አሻራወች አልገለጸም?? ምሳሌ በተስፋየ ገብረአብ የልብወለድ ታሪክ እነጃዋር ስላስሩት የአኖሌ ሀውልትና ሌላም ሌላም የታሪክ አሻራወች ካሉ እርሱ ራሱ ስለመጣበት ክልል መግለጽና መጥቀስ ነበረበት፡፡እውነቱ ግን የእርሱ አባቶች የአክሱምም ሆነ የዛጉየ እንደዚሁም የፋሲሊደስ ስልጣኔወች ወቅትና አሻራወች ላይ ተስትፎ አልነበራቸውም ሳይሆን በቦታው ላይ አልነበሩም፡፡ ሀቁ ይሄ ነው፡፡

ወደ ርእሳችን እንመለስ፡ አብይ በአመዛኙ በሆዳሞቹ የአማራ ሹመኞች እሽኮለሌ ባይነት ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ የስልጣን ኮርቻ ከመቆናጠጡ በፊት “እርካብና መንበር”

በሚለው መጽሀፉ ላይ ስልጣን እንዴት በሴራ፣ በተንኮልና በማጭበርበር እንደሚያዝ ጽፏል፡፤ በዚህ መልክ አንዴ ስልጣን ላይ ከተወጣም በኋላ እንዴት አድርጎ ህዝብን በዘርና በጎሳ ለያይቶ፣ በምላስ አታልሎ፣ በቁራሽ ስልጣንና በማይረባ ጥቅም ደልሎ፣ አንዱን ከአንዱ ከፋፍሎ፣ በጉልበት ረግጦ፣ እርስ በእርስ አናክሶና፣ አባልቶ የአገዛዝ ዘመንን ማራዘም እንደሚቻል ተንትኖ ጽፏል፡፡ አሁን እየሰራ ያለው ያንን ነው፡፡

አብይን << ..ይህ ለአንተም በስልጣንህ መቆየት፣ ለአገሪቱም አንድ መሆንና ለህዝቡም ኑሮ የሚበጅ ድርጊት፣ እቅድና እርምጃ አይደለምና ይቅርብህ አታድርገው …>> ብሎ የሚመክረው አንድም ነጻ አእምሮ ያለው ሀቀኛና ሚዛን የሚደፋ ሰው በአጠገቡ የለም፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት አብይ ራሱ ይህ አይነቱ ሰው በአጠገቡ እንዳይኖር አስቀድሞ አሳምሮ ሰርቷልና ነው፡፡

ስለሆነም አብይ በዙሪያው የኮለኮላቸው በሁለት ምድብ ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ፡፡ በትልቁ ምድብ ውስጥ ያሉት በኦሮሙማ አክራሪነት የተሰባሰቡ አደገኛና ተረኛ የኬኛ ጅቦችን ሲሆን በአናሳ ቁጥር በሁለተኛዋ ምድብ ውስጥ ደግሞ ውርውር የሚሉት ሆዳም የአማራ ሹመኛ ተብየወቹ ናቸው፡፡፡ ከዚህ ውጭ ያሉት ከየክልሉ የሰበሰባቸውና በብልጽግና ፓርቲ ማህበር “”ጠበልተኞች”” ያደረጋቸው እዚህ ግቡ የማይባሉ ለማናጀነት ከየክልሉ በኮታ የሰበስባቸው ናቸው፡፡

በኩርፊያ ርቆ የቆየው የትግራዩ የወያኔ ቡድን መደረግ ካልነበረበት ሰቅጣጭ ጦርነት በኋላ አሁን ወደ ኦሮሙማ መስመር ለመግባት እየተዘጋጀ ነው፡፡ ወያኔ በዚሁ የማስመስልም ይሁን ወይንም ሌላ ምርጫ የማጣት ሁኔታ ተግድዶም ሆነ ወድዶ ባሰላው ስሌቱ ወደ ፌደራል መንግስት አካልነቱ እየተመለሰ ይመስላል፡፡

ይህ ክስተት አብይ አህመድ ኢትዮጵያ ተመልሳ ወደ ዱሮው ጥንካሬዋና የነጻነት ቀንድል የመሆን አገርነቷ እንዳትመልለስ የሚጥረው የምእራቡ አለም ዋና ተጠሪ በሆነችው በአሜሪካ ቀጥተኛ ትእዛዝ ከወያኔ ጋር የፈጸመውን አሳፋሪ የፕሪቶርያ ስምምነት ይበልጡኑ በሚያሳፍር መልኩ ስምምነት ተብየውን በአገርና ህዝብ ላይ የተሰራ ፌዝ ይበልጡኑ አፈር ከድሜ ያስገባ ክስተት ነው፡፡

ወያኔ የእስካሁኑ በሀይል የአማራ መሬቶችን በሀይልመልሶ የመውሰድ ሙከራወች ሁሉ ስላልተሳኩለት ምሳሌ ቅራቅር ላይ የገጠመው የአማራ ሀይሎች ድል አድራጊነት>> በፌደራል መንግስት “የሰላም እርምጃወች ”በሚለው የማጨናበሪያ አንቀልባ ታዝሎ የአማራ ህይልን ትጥቅ በማስፈታት የአማራ ርስቶች የሆኑትን ወልቃይትንና ራያን መልሶ ለመውሰድ አቆብቁቧል፡፡

አብይ አህመድ የአማራን ሀይል ድጋፍ በሚሻበት ወቅት ብቅ ብሎ “ቤገምድሬ” ለራሱ አያንስም ይለናል፤፡ እጅግ ሰቅጣጭና እጅግ ዘግናኛ የሆነውን በሳምሪ ታጣቂወች በአማራወች ላይ በማይካድራ የተፈጸመውን የወያኔ ጭፍጨፋን

በሚመለከትም አብይ አህመድ ሲያብራራ "የማይካድራው ጭፍጨፋ ማንም ያላልተናገረለት፣ ማንም ያልዘገበውና የማያነሳው በታሪክ ወደር የሌለው ጭፍጨፋ ነው" ይለናል፡፤ አብይ ጅኒው ሲመጣበት ብቻ ሳይሆን አለቆቹ አሜሪካኖቹ<< .. " ዋ " ያችን የምታውቃትን የወንጀለኝነት ፋይልህን እንመዛትና…> ሲሉትና ወይንም ይሉኛል ብሎ ሲንቦቀቦቅ ደግሞ ወልቃይትንና ራያን ለወያኔ ለማስረከብ በ31 ዙር ስልጥኖና የአገሪቱ መከላከያ ሰራዊት ያልታጠቃቸውን ከተዋጊ አውሮፕላኖች ውጭ ያሉትን እጅግ ዘመናዊ መሳሪያወች እስከ አፍንጫው ድረስ የታጠቀውን ከ300 ሽህ በላይ የኦሮሞ ልዩ ሀይል ጫፉ እንዳይነካ ተደርጎ የአማራ ልዩ ሀይል እንድፈርስ ወስኗል፡ ፡ ውሳኔውንም ለመተግበር እንደ ጀኔራል አበባው ታደሰ ያሉት አሳፋሪ የአማራ ጄነራልንና መሰሎቹን ልኮ አማራውን ትጥቅ ለማስፈታት እየሰራ ነው፡፡

የአማራ ህዝብ ሆይ፡- ወልቃይትና ራያ ታሪካዊ ርስቶችህ ናቸውና ወያኔወች በዉጊያ ሞክረውህ ሳይሳካላቸው ሲቀር በእጅ አዙር ትጥቅህን ፍታና ርስቶችህን ወያኔወች ይውሰዷቸው የሚሉህን ዘወር በሉ በላቸው፡፡ ወልቃይትና ራያ የአማራ ርስቶች መሆናቸውን ሚሊዮን የታሪክና የተግባር ማሳያወች አሉ፡፡ ሲጀመር ወልቃይት ብሎ፣ ተከዜ ብሎ፣ ግጨው ብሎ የትግሬ የቦታ ስም የለም፡፡ ራያ ብሎ፣ አለማጣ ብሎ ፣ ኮረም ዋግ፣አፍላ ወዘተ ብሎ የትግሬ የቦታ ስም የለም፡፡